# የኤርትራና-ጅቡቲ የሰላም ስምምነት ሲፈተሽ

መለስ ዓ.

ዳንኤል ገብራይ አዲስ አበባ ውስጥ ተወልዶ ያደገ ኤርትራዊ ነው:: ድህረ-ኤርትራ ነፃነት ወደ አገሩ ቢሄድም የገጠመው በኃይል ታፍሶ ወደ ሳዋ መግባት ነበር:: ኤርትራ በሀገራችን ላይ ጦርነት አውጃ ወደ ሙሉ ውጊያ በተገባበት ወቅት በኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ተማርኮ ማይቀነጣል (ትግራይ) እና ደዴሳ ውስጥ በነበሩ የምርኮኛ ጣቢያዎች ቆይታ ካደረገ በኋላ ጦርነቱ በመቆሙ ወደ አገሩ ቢመለስም ህይወት በቀላሉ አልተቀበለችውም:: በድጋሚ የአስመራ ነዋሪዎች "ነበር" ሰፈር የሚሉትና ከኢትዮጵያ የሄዱ ኤርትራውያን በሚሰባሰቡበት አካባቢ /ኤርትራዊያኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ጋራዥ ነበረኝ፣ ቪላ ነበረኝ፣ ፋብሪካ ነበረኝ ስለሚሉ የተሰጠ ስም ነው/ ሲዘዋወር ተይዞ ወጣት ምልምሎችን (ዋርሳ ይካአሎ) ለመቀላቀል ተገደደ:: ከዚህ በኋላ ዳንኤል ሀገሩን ጥሎ የሚሄድበትን መንገድ ሲያስብ ከቆየ በኋላ ለቅኝት እንደወጣ ከመሰል ወታደሮች ጋር ወደ አገራችን ተሰዷል:: ዳንኤል ትግራይ ማይአይኒ ስደተኞች ካምፕ ቢኖርም ተወልዶ ያደገባትን የአራት ኪሎ ቅድስት ማርያም አካባቢ እየመጣ ከቀድሞ ጓደኞቹ ጋር ጊዜውን ያሳልፋል::

ይህን የአንድ ኤርትራዊ ቅጣት ሺዎች ይጋሩታል:: የኤርትራ መንግስት ወደ ኢትዮጵያ የሚሸሹ እንዲገደሉ፤ ወደ ሱዳን የሚሄዱ ደግሞ ቢያንስ እንዲታሰሩ ቢልም ፍልሰቱን ማስቆም አልቻለም:: የኤርትራ መንግስት ኢትዮጵን ሲያል የሚያስመስል ዘገባ በመገናኛ ብዙሃኑ በየዕለቱ ኢሬቲቪ ቢያስተላልፍም ዛሬም ኢትዮጵያ መሸሸጊያቸው ናት:: መረጃዎች እንደሚያሳዩት እስካሁን 51ሺ ያህል ኤርትራውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል:: ከእነዚህም ውስጥ አራት ሺ በላይ ወታደሮች ናቸው:: ወደ ሌሎች የአካባቢው ሀገሮች የሚሰደዱትን ደግሞ ቤታቸው ይቁጠራቸው:: ታዋቂው ሶሽዮሎጂስት ሮበርት ኬ.ሜርቶን አምባገነንነት በሰፈነባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ህዝቡ በደስታ ማጣት፣ የህይወት ዋስትና አለመኖር፣ ለፀፀት እና ለድብርት ይጋለጣል ይላሉ:: በዚህም ሳቢያ አገር ጥሎ ስደት ዋነኛውና ብቸኛው አማራጭ እንደሆነ ያስረዳሉ:: የኤርትራ መንግስት በተከተለው የተሳሳተ ፖሊሲ ሳቢያ ህዝቡ ለመከራ ሲጋለጥ ሀገሪቱም ከቀረው ዓለም ተነጥላለች:: ከወጣቱ ውስጥ 36 በመቶው ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ በተለያዩ የስነ አዕምሮ በሽታ የተጠቃ ነው:: ኤርትራ ትልቅ እስር ቤት ሆናለች:: ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ለዚህ ተጠያቂ የሚያደርጉት የአሜሪካ የስለላ ድርጅት /ሲ.አይ.ኤ/ን ሲያልፍ የፈረደባት ኢትዮጵያ ነው:: የችግሩ መነሻም መድረሻም ግን እሳቸው የሚመሩት መንግስት ነው::

ጭር ሲል አልወድም!

ኤርትራ ትንሽ አገር ናት:: ኢኮኖሚዋ ደካማ ነው:: በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የህዝቡን ህይወት መለወጥ አልቻለም:: ከዚህ በተቃራኒ እንደተዋጊ በሬ ጋጣውን ማመስ ተግባሩ ነው:: ሁሉም አገሮች ላይ ጦርነት አውጆ አካባቢውን አምሷል:: ይህ ሲያቅተው ደግሞ ጎረቤቶቹን ተቃዋሚዎቻቸውን በማስታጠቅ በእጅ አዙር ይወጋል:: ለኤርትራ እስከጠቀመ ድረስ ከአልቃይዳ ጋር ያብራል:: አስመራ የሶማሊያ፣ ኢትዮጵያ፣ ሱዳን፣ ቻድ ... ወዘተ አማፅያን መቀመጫ ናት:: የኤርትራ መንግስት ተቃዋሚዎችን ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ በገንዘብም በመሳሪያም ይረዳል:: ከእሱ ፍላጎትና ፈቃድ ለመውጣት የሞከሩትን ደግሞ ያስራል:: ይህ የኤርትራ መንግስት ድርጊት በአካባቢው ብቻ የተወሰነ አይደለም:: ኮሎምቦ ታይምስ የተባለ የስሪላንካ ጋዜጣ እንደዘገበው ኤርትራ የታሚል ታይገርስ አማፂ ቡድንን በመሣሪያ ስትደግፍ ኖራለች:: ቀደም ሲል የአስመራ ዩኒቨርሲቲ መምህር የነበሩት መሀመድ ኪያር ኡመር የኤርትራ መንግስት የአፍሪካ ቀንድ የትርምስ ኃይል ነው ሲሉ ይገልጹታል:: የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ዘጋቢ የሆነው ጄፍሬ ጀትልማን በበኩሉ የኤርትራ መንግስት የጦረኝነት አባዜ የተጠናወተው በመሆኑ ከጦርነት የሚያተርፍ /War Profitter/ እንደሆነ በአፅንኦት ያስረዳል:: እንደጋዜጠኛው አገላለጽ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ አገሩ ፀጥ ረጭ ሲል አይወዱም::

ብዙ ሰዎች የኤርትራ ኢኮኖሚ በተሽመደመደበት፣ ከሁከት በስተቀር ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ይህ ነው የሚባል ነገር በሌለበት፣ መንግስት ከእጅ ወደ አፍ የሆነውን የአርሶ አደር ምርት አስገድዶ እየገዛ ባለበት ሁኔታ ከየአገሩ የሰበሰባቸውን አማፅያን እንዴት መደገፍ፣ መደጎም ትችላለች? የሚል ጥያቄ ያነሳሉ:: ትክክለኛ ጥያቄ ነው:: ኤርትራውያን ከወር ደመወዛቸው እንዲያዋጡ የሚገደዱት የሁለት በመቶ ክፍያ አንደኛው የገንዘብ ምንጭ ነው:: እንደኛው አገር የደርግ ዘመን የእናት አገር ጥሪ መሆኑ ነው:: የኤርትራ መንግስት አለመረጋጋት ባለበት ሁሉ አለ፤ ይህን አጋጣሚ በመጠቀምም ካዝናውን ይሞላል:: ለምሳሌ በኮንጎ የእርስ በርስ ጦርነት ወቅት አልማዝና ወርቅ መዝብሯል:: ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አምባሳደር አንደብርሃን ገ/ሚካኤልን በኪንሻሳና ብራሰልስ (ከየት ወዴት እንደሚገናኙ ሀገራቱ ባይታወቅም) አምባሳደር በማድረግ በማይፈተሽ የዲፕሎማቲክ ከረጢት የሀገሪቱን ሃብት እንዳሻው በመዝረፍ ተግባር ተሰማርቶ ስነ ምግባር የጎደለው ድርጊት ሲፈፅም እንደነበር ይነገራል::

በደቡብ ሱዳን ውስጥ የኤርትራ ብሄራዊ ኢንሹራንስ ኮርፖሬሽን በሚል ኩባንያ በማቋቋም በስለላ ሰራተኞቹ አማካኝነት እየመዘበረ መሆኑንም ኒውቪዥን የተባለ የዩጋንዳ ጋዜጣ አስታውቋል። ኢንዲያን ኦሽን ኒውስሌተር የኤርትራ አገዛዝ ከመንግስትነት ተግባሩ ወጥቶ ወደ ኮሚሽን ወኪልነት ወርዷል ሲል ገልጾታል። ለዚህ ማሳያው የምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት /ኢጋድ/ ባለፈው ዓመት ያወጣው መግለጫ ነው። የኤርትራ መንግስት ለአልሸባብ እና ሂዝቡል ኢስላም ወኪል ሆኖ እንደተንቀሳቀሰ አመልክቷል።

የኤርትራ መንግስት ለተለያዩ አገሮች የተላላኪነት ሚና ይጫወታል። ኳታር፣ ሊቢያና ኢራን፣ ለሌሎች አገሮች ተቃዋሚዎች የሚያደርጉን ድጋፍ በማስተላለፍ ኤርትራ የፖስተኛ ስራ ትሰራለች፤ ከዚህም ኮሚሽን ይቆረጥላታል። በሶማሊያ ላይ የተጣለውን ማዕቀፍ የሚከታተለው አካል ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያቀረበው ሪፖርት ኤርትራ ከአንዳንድ ወገኖች ለአልሸባብ ይሰጥ የነበረውን ድጋፍ በማስፈጸም መስራቷን ይፋ አድርጓል። የታሚል ታይገርስ አማፂያን መርከቦች፣ ሃብትና ንብረት ስትጠቀም የነበረችው ኤርትራ የቀድሞው አማጺ ቡድን የፖለቲካ ክንፍ መሪዎች የመጨረሻ ምሽግ መሆኗን በመግለፅ የስሪላንካ መንግስት ኤርትራ በውስጥ ጉዳይዋ እንዳትገባ ለፀጥታ ጥበቃ ምክር ቤት አቤት እስከማለት ደርሳ ነበር። የኤርትራ መንግስት ለዚህ ክስ ብዙም ቁብ እንደሌለው አመልክቶ ስሪላንካ በአስመራ ኤምባሲ ለመክፈት ያቀረበችውን ጥያቄ ግን ውድቅ አድርጓል። የኤርትራ መንግስት በቅርቡ በኳታር ሸምጋይነት ታርቃለች የተባለችውን ጅቡቲ ተቃዋሚዎች አሰባስቦ ጥቃት ይፈፅማል። ፕሬዚዳንት ኢሳያስም ከትናንት የተማሩ አይመስሉም። ይህ ከመንግስታቸው ፖሊሲ በተጨማሪ ከግል ባህሪያቸው የመነጨ ሊሆን የሚችል ነው። ኤርትራ ውስጥ መንግስትም ተቃዋሚም ፕሬዚዳንቱ ናቸው። በኤርትራ ላይ ብዙ ጥናቶችን ያደረገው ዳን ከኔል ፕሬዚዳንቱ «የሚፈታተነኝ ሁኔታ ሲያጋጥመኝ ግትር እሆናለሁ። በባህሪዬም ስሜታዊ ነኝ» ማለታቸውን ጽፏል።

## <u>ጎልያድና ዳዊት</u>

በአሁኑ ወቅት አፍሪካ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶች ሶስት መልክ አላቸው። ሻለቃ ኢማና ሊናቡታ የተባሉ መኮንን በኬንያ ለናይሮቢ ዩኒቨርሲቲ የዓለም አቀፍ ግንኙነት የትምህርት ክፍል ባቀረቡት ጽሁፍ የእነዚህ ግጭቶች ዋና ዋና ምክንያቶች የስልጣን ፉክክር፣ ለተፈጥሮ ሃብት የሚደረግ እሽቅድምድምና በቀኝ ገዢዎች የተሰመሩ ድንበሮች ጉዳዮች ናቸው። ኤርትራ በድንበር ማካለል ሰበብ ኢትዮጵያን ብሎም የመንን ወግታለች። የድንበርን ጉዳይ በሰላማዊ መንገድ በክብ ጠረጴዛ መፍታት ሲቻል ወደ

ጦርነት የመግባት አባዜ ግን ጤነኝነት አይደለም:: ዊልያም ዛርትማን የተባሉ ተመራማሪ «ግጭትና ጣልቃ ገብነት» በሚል ርዕስ ባቀረቡት ፅሁፍ የትኛውም ሀገር ከፈለገ ከሌላው ሀገር ጋር ከድንበር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ችግሮችን መቀስቀስ ቢችልም በዚህ በማሳበብ ወደ ጦርነት አለመግባት ይሻላል ይላሉ:: ይህ ምክር ኤርትራን አይመለከትም:: በየመን የጀመረችውን በኢትዮጵያ የቀጠለችውን ወረራም ከሁለት ዓመት በፊት ጅቡቲ ላይ ፈፅማለች::

ጅቡቲና ኤርትራ 110 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያላቸው የጋራ ድንበር ይጋራሉ:: ሁለቱ አገሮች ከመልክዐምድር መቀራረብ በተጨማሪ ጠንካራ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት አላቸው:: ይሁን እንጂ በኤርትራ መንግስት ጦር አምላኪነት ሳቢያ ሶስት ጊዜ ወደ ጦርነት የተቃረበ ሁኔታ ውስጥ ገብተዋል:: በተለይም በ1988 ዓ.ም ኤርትራ ራስዱሜራ አካባቢን በመደብደቧና በመቆጣጠሯ ወደ ከፍተኛ ግጭት ሊገቡ ችለው ነበር:: አንዳንድ ወገኖች የወቅቱ ችግር የተፈጠረው ኤርትራ አካባቢውን በካርታዋ ውስጥ በማስገባቷ እንደነበር ይጠቅሳሉ:: ይሁን እንጂ በጅቡቲና ኤርትራ መካከል የተፈጠረው መፋጠጥ እንደአሁን የዓለምን ትኩረት የሳበበት ወቅት አልነበረም::

የኤርትራ መንግስት በሀገራችን ላይ ወረራ በፈፀመበት ወቅት ጅቡቲ ከኢትዮጵያ ጎን ቆማለች በሚል ያቄመበት ጊዜ ነበር:: በወቅቱ የቀድሞ የጅቡቲ ፕሬዚዳንት ሀሰን ጉሌድ ኦፕቲዶን ለመሸምገል ቢሞክሩም ኤርትራ ገለልተኛ አይደሉም ብላ ጥረታቸውን አልተቀበለችውም:: ፕሬዚዳንቱ በወቅቱ ከእፎይታ መጽሄት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ዋጋዱጉ ቡርኪናፋሶ ውስጥ ተካሂዶ በነበረው የሰላም ውይይት ከአንድ የሀገር መሪ በማይጠበቅ መልኩ ዘልፈውኛል ሲሉ ተናግረዋል:: ከዚህ ሁኔታ በኋላ ኤርትራ አምባሳደሯን ጠራች:: በጊዜው ውጥረቱን ያከረረው ሌላ ጉዳይ ጅቡቲ የኢጋድ ፀሐፊ የነበሩትን ኤርትራዊ አቶ ተከስተ ገብራይ ወደ ሀገሯ እንዳይገቡ መከልከሏ ነበር:: ከዚህ ፖለቲካዊ ሁኔታ በተጨማሪ ሁለቱን ሀገሮች ያጋጨው ጉዳይ ኢትዮጵያ የጅቡቲን ወደብ በመጠቀሟ ሳቢያ ሀገሪቱ ያገኘችው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ኤርትራን በማስቆጣቱ ነበር::

አሜሪካ ጅቡቲ ውስጥ የከፈተችው የጦር ሰፈር ኤርትራ ሀገሯ ውስጥ እንዲሆን ግሪንበርግ የተባለ የአሜሪካ ተቋምን ለአንድ ዓመት በወር 50 ሺ ዶላር በመክፈል ብታሰራም አሜሪካኖቹ ጥያቄውን አልተቀበሉትም:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ኤርትራ የኢንቨስትመንት ዕድል እና የፀጥታ ዋስትና ለማግኘት የነበራት ህልምም አብሮ መክኗል:: አሜሪካ ጥያቄውን ያልተቀበለችው በፕሬዚዳንቱ የማይታመንና ተለዋዋጭ

ባህሪ እና ከኤርትራ ጋር በመሞዳሞድ ኢትዮጵያን ማጣት ስለማትፈልግ እንደሆነም ተንታኞች በወቅቱ ገልጸዋል፡፡ሁለቱ ሀገሮች በ1992 ዓ.ም ቢታረቁም መሠረት ነው ያሉት ሠላማዊ ግንኙነት ከአስር ዓመት በላይ አልዘለለም፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት ኤርትራ ጅቡቲን ወረረች፡፡ ወታደሮቿም የራስ ዱሜራ ኮረብታና ሀይቅ ያዙ ተባለ፡፡ ጅቡቲዎች ኤርትራ ለመንገድ መስሪያ የሚሆን አሸዋ ለመውሰድ በሚል ወታደሮቿን አስገብታ በኃይል አልወጣም እንዳለች ተነግረዋል፡፡ ይህን የጅቡቲ ክስ ኤርትራ አልተቀበለችም፡፡

አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ይህ የኤርትራ ወረራ መነሻ ራስ ዱሜራ ሳይሆን የሶማሊያ ጉዳይና ከዚያ ባሻገር ነው ይላሉ፡፡ ራስ ዱሜራ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታው የጎላ አይደለም፡፡ ጅቡቲ ከሌሎች ወገኖች ጋር በመሆን የሶማሊያ የሽግግር መንግስትና በሼክ ሸሪፍ ይመራ የነበረውን አልሸባብ ማደራደሯ ኤርትራ ጀርባዋን በስለት የተወጋች ያህል እንዲሰማት አድርጓታል ነው የሚባለው፡፡ ምክንያቱም የኤርትራ መንግስት ሶማሊያ ውስጥ መረጋጋት ካልጠፋ ከአስመራ ሞቃዲሾ የተዘረጋው የሽብር መረብ ይዳከማልና፡፡

የኤርትራ መንግስት ጅቡቲ ላይ ጦርነት በመክፈት ለሀገራችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመተላለፊያ ኮሪደር ሆኖ በሚያገለግለው የጅቡቲ መስመር ላይ አደጋ እንዲጋረጥ በማድረግ ኢትዮጵያ ላይ ጫና እንዲፈጠር የማድረግ ፍላጎት እንደነበረው ሲገለፅ ቆይቷል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በትንኮሳዎች እና የጠብ ጫሪ ድርጊቶች ሳይገፋ ከጀመረው የልማት ጥረት ሃዲድ ሳይወጣ በመቀጠሉ ይህ የኤርትራ ዕቅድ ላይሳካ ችሏል፡፡ ኤርትራና ጅቡቲ በወታደራዊ ቁመና ሲመዘኑ ዳዊትና ጎልያድ ናቸው፡፡ ለንደን የሚገኘው የዓለም አቀፍ ወታደራዊ ስትራቴጂ ጥናት ተቋም በ1997 ዓ.ም ያወጣው ሪፖርት ኤርትራ ወደ 200 ሺ ወታደር እንዳላት ሲገልፅ ጅቡቲ ያላት ወታደር 11 ሺ ያህል ብቻ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ሌሎች ወገኖች ይህን የኤርትራ ቁጥር ወደ 300 ሺ ያደርሱታል፡፡ በጦር መሣሪያ አቅምም ቢሆን ጅቢቲ በምንም መለኪያ ከአስመራ ጋር አትወዳደርም፡፡

ኤርትራ የጅቡቲን መሬት ከያዘች በኋላ ኢጋድ፣ የአፍሪካ ህብረት፣ የአረብ ሊግ ብሎም የመንግስታቱ ድርጅት ሁኔታው ወደነበረበት እንዲመለስ ቢጠየቁም የሚሰማቸው አልነበረም፡፡ ከዚህ ይልቅ የኤርትራ መንግስት የወረረው መሬት እንደሌለና ይህን የሚያስወሩት ጠላቶቹ እንደሆኑ በተደጋጋሚ በመግለፅ ሀቁን ለመሸፋፈን ሞክሯል፡፡ ኢትዮጵያ ጆርናል የተባለ ድረ-ገጽ እንዳሰፈረው የኤርትራ መንግስት «ከጅቡቲ ጋር ባለው ግንኙነት የኤርትራ አቋም» በሚል ርዕስ ለጸጥታው ጥበቃ ምክር ቤት በላከው

ደብዳቤ በሁለቱ አገሮች መካከል ምንም የድንበር ችግር የለም ብሏል፡፡ የማውቀው ነገር የለም ሲል የቆየው የአስመራው አገዛዝ ከሰሞኑ ደግሞ በኳታር አደራዳሪነት ወታደሮቹን ከጅቡቲ መሬት እንዳስወጣ አስታውቋል፡፡ ለጅቡቲ የደም ካሳ ለመክፈል በመስማማት ወራሪነቱንም አረጋግጧል፡፡ የኤርትራ መንግስት ኢትዮጵያ ላይ እንደፈፀመው እንኳ የካሳ ኮሚሽን ውሳኔ ብሎ ነገር አልጠበቀም፡፡ እዚህ በኤርትራ መንግስት ዘንድ መርህ ብሎ ነገር የለም፡፡ ለአንድ ቀን ፍጆታ እስከጠቀመ ድረስ መዋሸት ነውር አይደለም፡፡

የኤርትራ መንግስት ከጅቡቲ ጋር ለመስማማት የወሰነው የፀጥታ ጥበቃው ም/ቤት በውሳኔ ቁጥር 1907 መሠረት በወታደራዊና ከፍተኛ የፖለቲካ መሪዎች እና ከገዢው ፓርቲ ጋር የተያያዙ ኩባንያዎች ላይ የተጣለው የጉዞና የገንዘብ ማዕቀብና ዕገዳ አገሪቱን እንድትነጠል ስላደረጋት ነው የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ አገሪቱ ማዕቀቡ የተጣለባት ጅቡቲን ወርራ በመያዟ፣ ሶማሊያ ውስጥ ፀንፈኛ ኃይሎችን በመደገፍዋና ለአፍሪካ ቀንድ አለመረጋጋት መንስኤ ነው በመባሉ በመሆኑ የጅቡቲን ዶሴ ዕልባት በመስጠት ማዕቀቡ የሚነሳበትን ሁኔታ ማመቻቸት ሊፈልግ ይችላል፡፡

ሁለቱ አገሮች በግርድፉ የደረሱት ባለሰባት ነጥብ ስምምነት አንኳር ሃሳብ ኤርትራ ወታደሮቿን ታስወጣ፣ በመሬቱ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪወሰን ድረስ የኳታር የሠላም አስከባሪ ኃይል ይሰማራ፣ የምርከኞች እና የጠፉ ሰዎች ስም ልውውጥ ይካሄድ፣ የድንበር ማካለሉንም በአንድ ኩባንያ ቃል በቃል Global Company ይካሄዳል የሚል ነው፡፡ ይህ ብዙ ጥያቄዎችን ያጭራል፡፡ ይህ ካምፓኒ የኳታሩ አሚር ይሁን የማን አይታወቅም፡፡ በአንድ ካምፓኒ የተደረሰ ስምምነትስ እንዴት አሳሪ ሆኖ ተቀባይነትን ያገኛል? ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መሄድ ያልተፈለገውስ ለምን ይሆን? የኤርትራ መንግስት ይህን ተፈረመ ስለተባለው ስምምነት ለራሱ ህዝብ እንኳ ምንም ትንፍሽ ያለው ነገር የለም፡፡ የኤርትራ የመገናኛ ብዙሃን ስለጉዳዩ የዘገቡት ነገር የለም፡፡ ይህም ሌላ ጥያቄ እንድናነሳ ያደርገናል፡፡ የዳርፉር አማፅያንን አነስተኛ ውይይት የሚያራግበው የኳታሩ አልጀዚራስ ቢሆን ስለ ስምምነቱ በሰፊው አለመዘገቡ ለምን ይሆን? የጅቡቲ መንግስት በሉአላዊ መሬቱ ላይ ለመደራደር የተስማማው ረዥም ጊዜ የሚወስድ ውዝግብ ውስጥ የመግባት ፍላጎት ስለሌለው እንደሆነ ብዙ ተንታኞች ይስማማሉ፡፡ ስምምነቱ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ፕሬዚዳንት ጊሌ ኳታርን ከኤርትራ ጋር አስታርቂኝ ያሉበት ምክንያትም ይኸውነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ኤርትራ እንደልማዷ ፍሩድ የተሰኘውን አማፂ ቡድን አስታጥቃ ሰሜናዊ ጅቡቲ ውስጥ ጥቃት መፈፀም ጀምራለች፡፡ ቀደም ሲል ከጅቡቲ ፕሬዚዳንት

ባለቤት ኳድራ መሐመድ ጋር በሽርክና ሲሰሩ ቢቆዩም ከሀገር ተባረው ዶሃ ኳታር የሚኖሩት ቱጃር አብዱራህማን ቦሬ ተቃዋዎችን እንዲያሰባስቡ በመጠራታቸው ውሎ አዳራቸው አስመራ ሆኗል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፕሬዚዳንት ጌሌ በቅርቡ ህገ መንግስቱን በማሻሻል ለሶስተኛ ጊዜ በሚቀጥለው ዓመት መወዳደርና ማሸነፍ ይፈልጋሉና ውዝግቡ በሆነ መንገድ እንዲጠናቀቅ ቢፈልጉ አይገርምም፡፡

ከእነዚህ ጉዳዮች በተጨማሪ ግን ስምምነቱ እንዲፈረም የባህረሰላጤው አገር የሆነችው ኳታር ዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ ይዛ ተንቀሳቅሳለች፡፡ በዚህም ከኤርትራ ጋር እንደገና መቀራረብ ወይም አገሪቱን ከመገለል እንድትወጣ የሚፈልጉ ሌሎች ሀገሮችን ዕቅድ ተግባራዊ አድርጋለች፡፡

<u>የገንዘብ ዲፕሎማሲ</u>

ኳታር ኤርትራና ጅቡቲን በማቀራረብ ረገድ መሪ ተዋናይ ሆና ተጫውታለች፤አስፈጻሚዎቹም የሀገሪቱ አሚር እና ጠቅላይ ሚኒስትር ሼክ ሃሚድ ቢን ካሊፋ አልታኒ ናቸው፡፡ ኳታር በተለያዩ ወገኖች መሀከል ድርድር እንዲካሄድ በምታደርገው ጥረቷ ትታወቃለች፡፡ በ2000 ዓ.ም ለአረብ ሊግ፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እና ፈረንሳይ እምቢ ያሉትን የሊባኖስ ፖለቲከኞች አግባብታለች፡፡ በየመን መንግስትና ሁቲ አማፅያን፣ በዳርፉር ታጣቂዎችና የሱዳን መንግስት፣ በቻድና በሱዳን፣ ሊብያ ውስጥ ህፃናትን በኤች.አይ.ቪ ቫይረስ እንዲጠቁ አድርገዋል የተባሉ ቡልጋሪያውያን የህክምና ባለሙያዎች እንዲፈቱ ሸምግላለች፡፡ ፖል ሮክአወር የተባለ የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪ የአንጃ እና ግራንጃ ውዝግብ በማይጠፋበት የመካከለኛው ምስራቅ ቀጠና ኳታር ከአሜሪካ እና እስራኤል እስከ ሶሪያ እና ኢራን ብሎም ሂዝቦላህና ሃማስ ድረስ በማይታይ ቀጭን መስመር የተሣሠረ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አላት ይላሉ፡፡ ዋና ከተማዋ ዶሃ የአሜሪካኗን ካምፖዬቪድ ያህል የመደራደሪያ ቦታ ናት፡፡

የኳታር የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዋነኛ ግብ የባህረ ሰላጤውን አገሮች የትብብር መድረክ አላማን ማስፈፀም፣ በሀገሮች መሀከል አለም አቀፍ ውዝግቦች እንዲፈቱ ማድረግ እንደሆነ ይናገር እንጂ ፖሊሲው በአንድ ግለሰብ በጎ ፈቃድና ፍላጎት ላይ የተንጠለጠለ ነው፤ አገሪቱ ከአሚር ሼክ ሃሚድ ቢን ከሊፋ አልጃቢር አልታኒ የውጭ ጉዳይ ግንኙነቱ ምህዋር ናቸው፡፡ ኳታር አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ህዝብ ይኑራት እንጂ የአገሬው ተወላጅ ግማሽ ሚሊዮን እንደሚደርስ ይነገራል፡፡ ህዝቡ መሠረታዊ ፍላጎቱ ብቻ ሳይሆን ሌላም ምድራዊ ህልሙ የተሟላ በመሆኑ በጋዝ ምርትና ነዳጅ የምትታወቀው ኳታር

ያላትን ገንዘብ የምታደርግበት አጥታለች፡፡ በዚህም ሳቢያ ኳታር በተለያዩ ወገኖች መሀከል የተሳካ ድርድር እንዲፈፀም በማድረግ ቀደም ሲል በመካከለኛው ምስራቅ ጉልህ ሚና የነበራቸውን ሳዑዲ አረቢያና ግብፅ በልጣለች፡፡ አለን ሄኔሪክሰን የተባለ የፖለቲካ ሳይንስ ተንታኝ ኳታር እንደሌሎች አነስተኛ እና መካከለኛ ደረጃ የሚገኙና ወታደራዊ አቅማቸው የማያስተማምን አገሮች በአለም አቀፍ መድረኮች ጉልህ ገጽታ እንዲኖራቸው የማድረግን የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስትራቴጂ ትጠቀማለች ይላሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተቀናቃኝ ወገኖች ወደ መግባባት እንዲመጡ የገንዘብ ቼክ ይቆረጥላቸዋል፡፡ በዚህ የቼክ ቡክ ዲፕሎማሲ (Check book diplomacy) መሠረት የሊባኖስ ፖለቲከኞች 44 ሚሊዮን ዶላር ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሰላሳ የዳርፉር አማጽያን ከ60 ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደተሰጣቸው ይነገራል፡፡ ጅቡቲና ኤርትራስ? ጊዜው ሲደርስ ሊወጣ የሚችል ጉዳይ ቢሆንም የኳታር አሚር ያሉትን ወይም የሚወስኑትን ሁሉ እንቀበላለን ብሎ መግባባት ግን መስማማትን አይገልፅም፡፡ አለበለዚያ ሁለቱም ሀገሮች የሆዳቸውን በሆዳቸው ይዘው «እንሞክረው» ብለው ትዳር እንደሚመሰረቱ ጥንዶች ናቸው፡፡

ዶሃ በሚገኘው የጆርጅታውን ዩኒቨርሲቲ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ማርክ ፋራህ ኳታር በትምህርት፣ በሚዲያ፣ በስፖርት... ወዘተ መስኮች ሞዴል ሆና በመታየት በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ገዝፋ መታየት ትፈልጋለች ይላሉ፡፡ አልጀዚራ ቴሌቪዥን የዚህ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዘመቻዋ አካል ነው፡፡ በምዕራቡ ዓለም ሳይቀር ተፅዕኖዋ እንዲታይ ለማድረግ አልተቸገረችም፡፡ የግብፃዊው ቱጃር አልፋይድ ንብረት የነበረው የሃሮድስ ሱቆችን የግሏ አድርጋለች፡፡ በ2004 ይመረቃል ተብሎ የሚጠበቀው የለንደን ማማ ግንባታ ላይ ድርሻ አላት፡፡ በአጠቃላይ ለዚህ ስትራቴጂ ማስፈፀሚያ 70 ቢሊዮን ዶላር መድባለች፡፡ አገሬው ገንዘብ ይናገራል ይላል፡፡ እ.ኤ.አ በ2020 የዓለም ዋንጫን ለማዘጋጀት ፍላጎት እንዳላት ኳታር መግለፃ ይህን ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ ለማሳካት ያላትን ቁርጠኝነት ያሳያል፡፡

<u>ጎረቤት ይመረጣል?</u>

ኤርትራ በአጭር ዕድሜዋ ፖለቲካዋ በብዙ ውጥንቅጥ የተሞላ ነው፡፡ ወታደራዊ ፍጥጫ፣ ዲፕሎማሲያዊ መገለል እና የኢኮኖሚ መሽመድመድ መገለጫዎቿ ናቸው፡፡ ባለፉት 15 ዓመታት ኤርትራ ወርራ እንጂ ተወርራ አታውቅም፡፡ የመጨረሻዋ የዚህ ተጠቂ ጅቡቲ ናት፡፡ የፀጥታ ጥበቃው ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር 1907ን በኤርትራ ላይ ከመጣሉ በፊት በውሳኔ ሃሳብ ቁጥር 1862 አማካኝነት ኤርትራ ከጅቡቲ ትውጣ ቢልም አልተቀበለችውም፡፡ በመጨረሻም በኤርትራ ላይ ማዕቀብ ቢጥልባትም ጉዳዩ በቅን ልቦና

አይቶ ከመፍታት ይልቅ በሉዓላዊነቷ ላይ የተቃጣ እንደሆነ በመግለፅ ዜጎቿን ለማደናገር ኤርትራ ስትንቀሳቀስ ነበር፡፡ በኳታር አደራዳሪነት በተደረሰው ስምምነት ግን ወራሪነቱን አምኗል፡፡ ይህን ስምምነት ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በሙሉ ደግፏል፡፡ የአፍሪካ ህብት ኮሚሽነር ዣን ፒንግ በተለይ የዶሃው ስምምነት ሌሎች የሁለትዮሽ ውዝግቦችን ለመፍታት አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዳላት በመግለጽ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ውዝግብም ታስብበት የሚል እንድምታ ያለው ንግግር አድርገዋል፡፡ እዚህ ላይ ሁለቱ አገሮች ዕርቅ አውርደናል ቢሉ ማንም ጤነኛ ሰውም ሆነ ኃላፊነት የሚሰማው መንግስት አይጠላውም ብዬ አምናለሁ፡፡ ኢትዮጵያም የኤርትራ-ጅቡቲ ፋይል ቢዘጋ ትጠቀማለች እንጂ አትጎዳም፡፡ ይሁን እንጂ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ስምምነቱ ያልመለሳቸው ብዙ የግልጽነት ጥያቄዎች እንዳሉ መገንዘብ ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኤርትራ የተመድን የሰላም አስከባሪ ኃይል /አንሚ/ እንዲባረር በማድረግ በራሱ መሬት ላይ የነበረውን የፀጥታ ቀጠና በማፍረስ የአልጀርስ ስምምነትን ወረቀት ቀዶ በመጣል ለአለም አቀፉ ህግና አሰራሮች የማይገዛ መንግስት መሆኑን አሳይቷልና የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የጸጥታ ጥበቃ ምክር ቤት የጣለውን ማዕቀብ አጠንክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡ ጅቡቲን ጨምሮ በአፍሪካ ቀንድ ሰላም እንዲሰፍን የኤርትራ መንግስት በውጭ ጉዳይ የሚከተለውን ፖሊሲ (እሱም ካለ) ማስተካከል ይኖርበታል፡፡ በፔንሴልቬኒያ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ ኪዳኔ መንግስተአብ የኤርትራ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በደንብ ያልተጠና እና የተሳሳተ አቅጣጫ የሚከተል እንደሆነ ይከራከራሉ፡፡ በቅርቡ ተፈረመ የተባለው ስምምነት አንድ ነገር ሆኖ ውጤቱ ሌላ እንዳይሆን መጠንቀቅ ይገባል፡፡

ሳሊ ሂሊ የተባለች በለንደን የቻታም ሃውስ ተመራማሪ ደግሞ የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ማጠንጠኛ ኢትዮጵያ ናት ትላለች፡፡ በዚህ የተሳሳተ ፖሊሲ ሳቢያ የአካባቢው አገሮች ያለ መረጋጋት ስጋት ሊወገድ አልቻለም፡፡ ይሁን እንጂ ጓደኛ ቢመረጥም ጎረቤት አይመረጥምና እኛን በተመለከተ በያዝነው የሰላምና የልማት አቅጣጫ መፅናት የግድ ይላል፡፡